የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

አሥራሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፴፩
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

12th Year No. 31
ADDIS ABABA 29th June , 2006

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፬፻፺፭/፲፱፻፺፰ ዓ.ም

የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲን እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ… ገጽ ፫ሺ፬፻፳፭

**CONTENTS**

**Proclamation No. 495/2006**
Social Security Agency Re-establishment Proclamation …. Page 3425

## አዋጅ ቁጥር ፬፻፺፭/፲፱፻፺፰

## የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ተግባሩን በብቃት ለማከናወን በሚችልበት ሁኔታ እንደገና ማደራጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲን እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፬፻፺፭/፲፱፻፺፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. መቋቋም

፩/ የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ /ከዚህ በኋላ "ኤጀንሲ" እየተባለ የሚጠራ/ የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል፣

፪/ የኤጀንሲው ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል።

፫. ዋና መሥሪያ ቤት

የኤጀንሲው ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ስፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 495/2006.

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE RE-ESTABLISHMENT OF THE SOCIAL SECURITY AGENCY

**WHEREAS,** it is necessary to reorganize the Social Security Agency in such a way as to enable it to perform its duties efficiently;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) of the Constitution, of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows;

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "Social Security Agency Re-establishment Proclamation No.495/2006."

### 2. Re-establishment

1/ There is hereby re-established the Social Security Agency (hereinafter "the Agency") as an autonomous federal agency having its own juridical personality.

2/ The Agency shall be accountable to the Prime Minister.

### 3. Head Office

The Agency shall have its Head Office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere as necessary.

**፬. ዓ ላ ማ**

የኤጀንሲው ዓላማ የማህበራዊ ዋስትና ፕሮግራሞች እንዲጠናከሩና እንዲስፋፉ ማድረግ ይሆናል::

**፭. ሥልጣንና ተግባር**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

፩/ የማህበራዊ ዋስትና ሕጎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን በሥራ ላይ ያውላል፣

፪/ የማህበራዊ ዋስትና መዋጮ አሰባሰብ ሥርዓት ይዘረጋል፣ መዋጮ ይሰበስባል፣ አሠሪ መሥሪያ ቤቶች ሥርዓቱን ተግባራዊ ማድረጋቸውን ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊ ሲሆን ሰነዶችንና መዛግብትን አስቀርቦ ወይም በአሠሪ መሥሪያ ቤቶች ተገኝቶ ይመረምራል፣

፫/ የማህበራዊ ዋስትና ፈንዶችን ያስተዳድራል፣

፬/ ለማህበራዊ ዋስትና መብት ብቁ የሚያደርጉ ማስረጃዎችን በቅድሚያ አሰባስቦ ይይዛል፣

፭/ መዋጮ በወቅቱ በማይከፍሉ፣ የጡረታ መዋጮ ሂሣብ መዝገብ በማይዙ፣ ማስረጃ በማይልኩ እና መረጃ በማይሰጡ አሠሪ መሥሪያ ቤቶችና ግለሰቦች ላይ ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል፣

፮/ የማህበራዊ ዋስትና መብትን ለማስከበር የሚቀርቡ ማስረጃዎችን ብቃት፣ የጥቅም ዓይነት እና መጠኑን ይወስናል፣ ክፍያ ይፈጽማል፣

፯/ በማህበራዊ ዋስትና መብትና ጥቅም ጥያቄዎች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣

፰/ የማህበራዊ ዋስትና ፈንድን ትርፋማና አስተማማኝ በሆኑ የኢንቨስትመንት ሥራዎች ላይ ያውላል፣

፱/ የማህበራዊ ዋስትና ፈንዶች በየተወሰነ ጊዜ በሂሳብ ስሌት አዋቂዎች /አክቹዋሪ/ እንዲጠኑ ያደርጋል፣

፲/ የማህበራዊ ዋስትና ሽፋንና ፕሮግራሞች ስለሚጠናከሩበትና ስለሚስፋፉበት ሁኔታ ጥናት እያካሄደ ለመንግሥት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣

**4. Objective**

The objective of the Agency shall be to strengthen and expand social security programs.

**5. Powers and Duties**

The Agency shall have the powers and duties to:

1/ implement social security laws, regulations and directives;

2/ establish a system for the collection of social security contributions and collect the social security contributions; ensure that every employer implements the system; inspect related records and documents where necessary by requiring their submission to it or by visiting the premises of employers;

3/ administer social security funds;

4/ collect in advance and maintain records of evidentiary data that entitle persons to social security benefits;

5/ take legal actions against employers and individuals who fail to pay social security contributions, establish contributions record system and to furnish required documents or information on time;

6/ determine the adequacy of entitlement claims evidentiary documents, the types and amount of social security benefits to which a beneficiary is entitled, effect payment of benefits;

7/ decide on claims related to social security rights and benefits;

8/ invest the social security funds in profitable and reliable investment activities;

9/ cause periodical actuarial study and review of the social security funds;

10/ undertake studies to strengthen and expand social security programs and coverage, submit it to the government and implement same upon approval;

፲፩/ በሥልጣንና ተግባሩ ሥር የሚካተቱ ጉዳዮችን በሚመለከት የሥራ አፈጻጸም መመሪያዎችን ያወጣል፣

፲፪/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፣

፲፫/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል::

## ፮. የኤጀንሲው አቋም

ኤጀንሲው፣

፩/ የሥራ አመራር ቦርድ /ከዚህ በኋላ “ቦርድ” እየተባለ የሚጠራ/፣

፪/ በመንግሥት የሚሾሙ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣ እና

፫/ አስፈላጊ ሠራተኞች፣

ይኖሩታል::

## ፯. የቦርዱ አባላት

፩/ የቦርዱ ሰብሳቢና አባላት በመንግሥት ይሰየማሉ፣ ቁጥራቸውም እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል::

፪/ የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር የቦርዱ አባልና ፀሐፊ ይሆናል::

## ፰. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

፩/ ቦርዱ የኤጀንሲውን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ፣

ሀ/ የኤጀንሲውን ስትራቴጂ፣ ዕቅድ፣ በጀትና የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ያጸድቃል፣

ለ/ የጡረታ ዕቅዱንና ፈንዱን የሚመለከቱ አጠቃላይ የፖሊሲ ጉዳዮችን ለመንግሥት አቅርቦ ያስወስናል፣

ሐ/ የኤጀንሲውን የሠራተኛና፣ የንብረት፣ የፋይናንስ ሥራ አመራርና ሌሎች አስተዳደር ነክ መመሪያዎች ያወጣል፣

መ/ የኤጀንሲውን ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሥራ ደረጃ ምደባ፣ የደመወዝ ስኬል፣ ጥቅማ ጥቅምና የአበል መጠን ይወሰናል::

11/ issue directives on maters that come within its powers and duties;

12/ own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name;

13/ carry out such other activities as may be necessary for the fulfillment of its objective

## 6. Organization of the Agency

The Agency shall have:

1/ a Board of Management (hereinafter referred as to “the Board”);

2/ Director General and, as may be required, Deputy Director-Generals to be appointed by the Government; and

3/ the necessary staff.

## 7. Members of the Board

1/ Members of the Board, including the Chairperson, shall be appointed by the Government with their number to be determined as necessary.

2/ The Director General of the Agency shall be member and secretary of the Board.

## 8. Powers and Duties of the Board

1/ The Board shall, as the superior body, direct and supervise the activities of the Agency.

2/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (1) of this Article the Board shall have the powers and duties to:

a/ approve the strategy, plan and budget of the Agency;

b/ submit general policy maters regarding social security schemes and funds to government for approval;

c/ approve personnel, property, financial management and other administrative directives of the Agency;

d/ decide on the organizational structure, position classification, salary scale, benefits and allowance rates of the Agency.

## ፱ የቦርዱ ስብሰባ

፩/ ቦርዱ በሦስት ወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፣ ሆኖም አስፈላጊም ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፡፡

፪/ በቦርዱ ስብሰባ ላይ አብዛኞቹ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

፫/ የቦርዱ ውሳኔ የሚተላለፈው በስብሰባው ላይ ከተገኙት አባላት በአብዛኛው ድምጽ ሲደገፍ ነው፡፡ ሆኖም ድምጹ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

፬/ ቦርዱ የራሱን የአሠራር ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፲. የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ ቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የኤጀንሲውን ሥራዎች ይመራል፣ ይቆጣጠራል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፣

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ የተመለከተውን የኤጀንሲውን ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ ያውላል፣
ለ/ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የኤጀንሲውን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፣
ሐ/ የኤጀንሲውን ስትራቴጂ፣ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣
መ/ ለኤጀንሲው በተፈቀደለት በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣
ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኤጀንሲውን ይወክላል፣
ረ/ የኤጀንሲውን የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ለሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ያቀርባል፡፡

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለኤጀንሲው ሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለኤጀንሲው ኃላፊዎችና ሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

## 9. Meetings of the Board

1/ The Board shall meet once in three months; provided, however, that it may meet at any time as may be required.

2/ There shall be a quorum where more than half of the members are present at a meeting of the Board.

3/ Decisions of the board shall be passed by a majority vote of the members present at a meeting. In case of a tie, the chairperson shall have a casting vote.

4/ The Board may adopt its own rules of procedure.

## 10. Powers and Duties of the Director General

1/ The Director General shall be the chief executive officer of the Agency and shall, subject to the general directives of the Board, direct and control the activities of the Agency.

2/ Without limiting the generality stated in Sub-Article (1) of this Article, the Director General shall:

a) exercise the powers of the Agency specified in Article 5 of this Proclamation;
b) employ and administer employees of the Agency and decide the termination of their service in accordance with directives to be issued by the Board;
c) prepare and submit to the Board the strategy, plan and budgets of the Agency and implement same upon approval;
d) effect expenditure in accordance with the approved budget of the Agency;
e) represent the Agency in all its dealings with third parties;
f) submit reports of the Agency to the concerned government bodies.

3/ The Director General may delegate part of his powers and duties to the officials and other employees of the Agency to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Agency.

**፲፩. <u>የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ</u>**

፩/ የማህበራዊ ዋስትና መብትና ጥቅምን በሚመለከት ኤጀንሲው በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርቡትን ይግባኞች እየመረመረ ውሳኔ የሚሰጥ የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ይቋቋማል፡፡

፪/ የጉባዔው አደረጃጀትና የአባላት አሰያየም በመንግሥት ይወሰናል፡፡

፫/ የይግባኝ አቤቱታ ለጉባዔው መቅረብ የሚችለው ይግባኝ በሚባልበት ጉዳይ ላይ ውሳኔ በተሰጠ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ነው፡፡

፬/ ጉባዔው ሥራውን የሚያከናውነው በጡረታ አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ይሆናል፡፡

፭/ ጉባዔው ይግባኝ የቀረበበትን የኤጀንሲውን ውሳኔ መለወጥ፣ ማሻሻል፣ ወይም ማጽናት ይችላል፣ ውሣኔውም የመጨረሻና የፀና ይሆናል፡፡

፮/ የጉባዔው ውሳኔ የሚተላለፈው በስብሰባው በተገኙ አባሎች በአብዛኛው ድምጽ ሲደገፍ ነው፡፡ ሆኖም ድምጽ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

፯/ ጉባዔው የራሱን የአሠራር ሥነ ሥርዓት ደንብ ያወጣል፡፡

**፲፪. <u>በ ጀ ት</u>**

ኤጀንሲው ከጡረታ ፈንዱ በሚመደብ በጀት ይተዳደራል፡፡

**፲፫. <u>ስለሂሣብ መዛግብት</u>**

፩/ ኤጀንሲው የራሱን የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፣

፪/ የኤጀንሲው የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየዓመቱ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች ይመረመራሉ፡፡

**፲፬. <u>የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>**

፩/ የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፰/፲፱፻፹፰ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

**11. Social Security Appeal Tribunal**

1/ There shall be established a Social Security Appeal Tribunal which shall examine and decide on appeals made against decisions of the Agency relating to social security rights and benefits.

2/ The organizational structure of the Tribunal and designation of its members shall be determined by the Government.

3/ Appeal shall be made to the Tribunal within one year from the date of a decision against which the appeal is to be taken.

4/ The Tribunal shall decide all cases based on the provisions of relevant Pension Proclamation, regulations and directives.

5/ The Tribunal may reverse, vary or confirm decisions of the Agency against which appeals are taken. The decision shall be final and conclusive.

6/ Decisions of the Tribunal shall be passed by a majority vote of the members present at a meeting. In a case of a tie, the Chairperson shall have a casting vote.

7/ The Tribunal shall adopt its own rules of procedure.

**12. Budget**

The Agency's budget shall be allocated from the Pension Funds.

**13. Books of Accounts**

1/ The Agency shall keep its own books of accounts.

2/ The Books of accounts and other financial documents of the Agency shall be audited annually by the Auditor General or by auditors designated by him.

**14. Repealed and Inapplicable Laws**

1/ The Social Security Authority Establishment Proclamation No. 38/1996 is hereby repealed.

፪/ ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## ፲፭. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

2/ Any law inconsistent with the provisions of this Proclamation shall have no effect on maters provided for by this Proclamation.

## 15. Effective Date

This Proclamation shall come in to force up on publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 29th day of June, 2006.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**